# PANORAMA # XVIX

## <u>የትዝብት አድማስ</u>

*መጋቢት* 26 2000

## <u>*በአንድ ልሳን የማይናገር ሕዝብ የሚያጻምጠው አያገኝም*</u>

*የሀገራችን ብሔራዊ ችግሮች የሁሉም ዜጋ የጋራ ጉዳይ መሆኑ ከታወቀ ዓመታት ያለፉ ቢሆንም፥የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ግን እስካሁን አልተቻለም። የሀገራችን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበረዊ ችግሮች ዓቢይና መሠረታዊ ምክንያት ያው ዞሮ ዞሮ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አለመስፈን መሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም፥ ብሔራዊ ችግሮቻችን ግን፥ አምባገነን ሥርዓትን በማስወገድ ብቻ የሚያከትሙ አይሆኑም። እነርሱን ለማስወገድ ደግሞ ከአድማስ ባሻገር ማየትን፥ ብሔራዊና ዘላቂ ዕቅድና ራዕይን በጋራ ነድፎ በጋራ ዓላማ ተሰልፎ ለጋራ ሀገር በጋራ መታገልን ይጠይቃል። ይህም ከተሳካልን፥ አንድ ሌላ መሠረታዊና ዘላቂ የሆነ ተግባር ይጠብቀናል። እርሱም <u>ሀገራችን ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጎቿ መኖሪያ</u> <u>ልትሆን የምትችልበትን ሥርዓተ-መንግሥት መመሥረት ነው።</u> የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፥ ዜጎቿ በሰላምና በነፃነት፥ በአንድነትና በእኩልነት፥በዕድገትና በብልፅግና የሚኖሩባት ሀገር አልሆነችም። ከዚህ በስተቀር፥ አሁን በሥልጣን ያለው ዘረኛ የአገዛዝ ብድን ሀገሪቱን በዕቅድ እያጠፋ ያለ እንጅ፥ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ሆኖ አልተገኘም። ይህ አልበቃ ብሎ፥የተቃዋሚ ኃይሎችና ሕዝቡ በአንድ አቅጣጫና ራዕይ የሚያማትሩ ሆነው አልተገኙም። ለዚህም መሠረታዊ ደንቃራ ከሆኑት መካከል ዋነኛው፥ የኢትዮጵያ የውጭና ሀገር በቀል ጠላቶቿ በመተባበር የሚያደርጉት ሴራ ነው። ታዲያ ይህንን ዓይነተኛ እንቅፋት ለማስወገድ የሚቻለው፥ ማነኛውም ዜጋ የተቃዋሚ ድርጅቶችም ጭምር፥ በአንድ አቅጣጫና በአንድ ብሔራዊ ራዕይ ዙሪያ ተሰባስበው ሲገኙ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ፥ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት፥ሰፍኖ ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና ይኬዳል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም። አሁንም አሁንም ሊሰመርበት የሚገባው፥የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላ በአንድ ልብ ሲነሳሳ፥ በአንድ ልሳን ሲናገርና በጋራ ሲቆም ብቻ ነው መፍትሄ የሚገኘው። ይህ ደግሞ ለጋራ ሀገርና ለሕዝብ ጥቅም በዕርግጥ ከልብ ማሰብ ከተጀመረ ከባድ አይሆንም።*

*የተቃዋሚ ድርጅቶችና ሌሎቹም የኅብረተ ስብ ክፍሎች በዕርግጥ ይህችን ሀገር ከጠቅላላ ጥፋት ለማዳን ከፈለጉ፥ በሚከተሉት መሠረታዊና ብሔራዊ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ተስማማምተው፥ በጋራ የተግባር አጀንዳ ነድፈው በጋራ መንቀሳቀስ መቻል አለባቸው። ይህ እስካሁን በሥራ ተተርጉሞ ታይቷል ለማለት አይቻልም። ሁሉንም በጋራ ሊያስተሳስሯቸውና የተባባረ*

ተግባር ሊፈፅሙ የሚያስችሏቸው መሠረታዊ ህቆች አሉ ብለን እናምናለን፡፡

እነርሱም፦

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ የማያወላውል አቋም መውሰድ፥ በጋራ መስማማት፥
- በሀገሪቱ የግዛት አንድነትና ብሔራዊ ነፃነት ላይ ሁሉም ዕምነቱን ማስረገጥ፥
- በሀገሪቱ ዜጎች ዕኩልነትና ሉዓላዊነት፥ የህግ የበላይነትና የሀገሪቱን ሀብት ሁሉም ዜጋ በዕኩል የመጠቀም መብትና ነፃነት እንዳለው ማመን፥ መስማማት፥
- የሀገሪቱን የነፃነት ልዕልና፥ የዜጎቿን አንድነትም ሆነ ሰላምና መረጋጋትን አስገኝቶ፥ወደ ልማትና የዕድገት ጎዳና ሊያመራ የሚያስችለው የዴሞክራሲ ሥርዓት ብቻ መሆኑን አምኖና ተስማምቶ በጋራ መታገልና መሥራት፥
- ሁሉንም ያላሳተፈ፥ያላካተተና ያላስተባበረ ትግል ግቡን እንደማይመታ በመረዳት፥ የጠነከረ ኅብረት ፈጥሮ የወያኔን ሥርዓት በጋራ ማስወገድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

እነኝህን ነጥቦች ዕውን አድርጎ ተጨባጭ ውጤት ለማስመዘገብ ከተፈለገ ደግሞ፥

1. ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች፥ እርስ በእርስ መነታረክንና መጠላለፍን ማቆም አለባቸው፡፡ ይህ ድርጊት ጨርሶ ማንንም አይጠቅምም፡፡ ወያኔ ግን ይደሰትበታል፡፡

2. የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ወዳጆችና ጠላቶች በሚገባ ተረድቶ አስፈላጊውን ጥንቃቄና ግንዛቤ መውሰድ ይገባል፡፡ የወያኔ መሪዎች ድርጊታቸው፥ የሀገራችን ጠላቶች እንጅ ወዳጆች እንዳላደረጋቸው መረዳት ያሻል፡፡

3. ከወያኔ ሰርጎ ገቦችና ሰላዮች ጥፋት መከላከል፥ እንቅስቃሴያቸውን በቅርብ እየተከታተሉ ማክሸፍ ለተቃዋሚ ድርጅቶች ትግል ወሳኝ እንደሆነ ያለማወላወል ማመን ይገባል፡፡ ጠላት ጠላት እንጅ ሌላ ሊሆን ከቶ አይችልም፡፡

እነኝህ ጉዳዮች የኢትዮጵያን ሕዝብና የተቃዋሚ ድርጅቶችን በአንድ ቃልና ልሳን እንዲናገሩ የሚያስችሏቸው ይሆናሉ ብለን እናምናለን፡፡ ዛሬ በብሔራዊ ጉዳይ ላይ ልብ ለልብ ተገናኝቶ ፥ ዐይን ለዐይን ተያይቶ፥ በአንድ ቃልና ልሳን መናገር ቢቻል ኖሮ፥ ትግሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ግብን መትቶ ወደ ልማትና የዕድገት ጎዳና ማምራት ይቻል ነበር ቢባል፥ የቀቢፀ-ተስፋ አነጋገር ሊሆን

አይችልም።

እስኪ ማንንም ሳይጠይቀን፥ ማንም ሳያሳስበንና ሳያስታውስን፥ እራሳችንን ጠይቀን እኛው እራሳችን ለራሳችን መልስ እንፈልግ። እናምጣ። የአያሌ ምዕተ ዓመት ታሪክ፥ የበለፀገ ባኅል፥ ነፃነትና ማንነት ያለን ሕዝቦች፥ እንዴት ዛሬ በሃያ አንደኛው ምዕተ-ዓመት ፥ ስለ ሀገር መኖርና አለመኖር፥ ስለ ዜግነታችን የማንነት ፍለጋ፥ በጋራ ሀገር በጋራ መኖር ወይም አለመኖር፥ ስለ ግዛት አንድነት መከበር/አለመከበር፥ ስለ ዜጎች የዜግነት ማንነትና ምንነት መጨነቅና መጠበብን፥ ስለ ኢትዮጵያ ብሔራዊና ዘላቂ ጥቅም ማሰብ እየቀረ፥ ስለ ጎጥና ቀበሌ መብተክተክ፥ በዕውነት ይገባን ነብርን? ስለአድነትና ኅብረት ቀርቶ፥ ስለ መለያየትና መበታተንስ መጨነቅስ ያስፈልጋልን? እነኝህንና ለሌሎችንም ተመሳሳይ ዘመን-አመጣሽና ሰው -ሰራሽ ችግሮች፥ ጥያቄዎችና አሳሳቢ ጉዳዮች በአንድ ላይ መፍታትና ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት፥ ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ ተግባርና ኃላፊነት አይደለም። ይህ ብሔራዊ ጉዳይ ለአምባገን መሪዎችና ነገ እንደጧት ጤዛ ለሚረግፉ ከፋፋዮች የሚተው ነገር አይደለም። ወይም ደግሞ፥ባዕዳን መፍትሄ እንዲያስገኙልን እነርሱኑ መለመን አይኖርብንም። <u>የማነኛው ሀገር ሕዝብ፥ የራሱን ችግር እራሱ መፍታት ካልቻለ ፥ ብሔራዊ ነፃነቱን፥ ሰብዕናውንና</u> <u>ማንነቱ ሁልጊዜ በጥያቄው ውስጥ እንደ አስገባ ይኖራል።</u> እኛም የራሳችንን ችግር መፍታት ካልቻልን፥ ከዚህ ክስተት ልናመልጥ አንችልም። ተወደደም ተጠላ፥ ይህን እንደ ኮሶ መድኅኒት የሚመር ፥ እንደ እንቆቆ የሚጎመዝዝ ሀቅ አምነን መቀበል ይኖርብናል። ለዕውነት ቆሜአለሁ የሚል ዜጋ ሁሉ ደግሞ መራራ ቢሆንም መደህኒትን ለመውሰድ ድፍረት ያጣል ብለን አናምንም። የኢሕአፓ አባላት እስካሁን በጽናት ቆመው እንዲታገሉ ካስቻላቸው ዓብነት፥መራራውን ሁሉ እየቻሉ መታገላቸው እንደሆነ ጠላትም ቢሆን የማይክደው ሀቅ ነው። የወያኔ መሪዎችም ቆሽታቸውን የሚያሳርርባቸው ይህ ሀቅ መሆኑን አምነው ተቀብለውታል። <u>ክተት መክት እያሉ በፅናት መታገል ኢሕአፓን ኢሕአፓ ካሰኙት ዋና ዋና ባኅርያት ኃይነተኛው ነው። ለዚህም ነው ወያኔዎቹ፥ በኢሕአፓ ላይ ያለ የሌለ ኃይላቸውን ለማሳረፍ የሚፍጨረጨሩት።</u> ግን ይህ ደግሞ የማይሳካላቸው መሆኑን በሚገባ ያውቁታል።

ዛሬ፦

- የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የዜጎቿን አንድነትና ነፃነት የሚያጠፋ ጠባብ ጎጠኛ አገዛዝ ሀገሪቱን ማጥፋቱን ቀጥሏል። መላው ሕዝብ ጠልቶትና ተቃውሞት፥ ንቆትና ደፍሮት በምርጫ ቢያሰወግደውም፥ በጥቂት ምዕራባውያን መንግሥታት ሁለንተናዊ ድጋፍና ትብብር ብቻ ተቀዋሚዎቹን እያጠፋ፥ እያሰረ እያሳደደና ሰላማዊውንም ሕዝብ፥ ህፃን፥ ሴትና ሽማግሌ ሳይቀር ባደባባይና በስውር መጨፍጨፉን ቀጥሎበታል።
- የኢትዮጵያ ሕዝብም በበኩሉ፥ አስፈላጊውን መሥዋዕት በመክፈል የተቃውሞ ትግሉን በየአቅጣጫው ቀጥሏል። ሕዝባዊውን ትግል ግን

አስተባብሮ የሚመራው አልተገኘም። ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ ተማሪዎችም እንደጥንቱ የሕዝብ ወገን መሆናቸውን ለማሳየት በመታገላቸው፥ በወያኔ ነፍሰ-ገዳይ ቡድኖች፥ እየተረሸኑ፥ እየታሰሩና እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ወጣቱ ትውልድ ቆራጥ ታጋይነቱን በማስመስከር፥ ማንኛውንም መስዋዕት ለመክፈል መዘጋጀቱን በተግባር እያሳየ መጥቷል። በብሔራዊ ደረጃ አስተባብሮ የሚመራው ካገኘ ደግሞ በአጭር ጊዜ ታምራዊ ውጤት እንደሚያስመዘግብ የታወቀ ነው።

- የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ተስፋ በሌለውና በማያንሰራራ ሁኔታ እየተንኮታኮተ ነው። የሥራ አጡን ቁጥር፥ በትክክለኛ አሀዝ መግለፅ የማይቻል ነው። የጎዳና ተዳዳሪው፥ የከተማ ነዶያኑና ምፅዕዋተኛውን ብዛት ለተመለከተ ሀገሪቱን ያዝንላታል እንጅ አያዝንባትም። የኑሮው ውድነት ሰማይ ጠቀስ ደርሷል። እጅግ በጣም ጥቂት የሆኑት የወያኔ ባለጊዜዎች ካልሆኑ በስተቀር፥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እርከን የሚገኘው ዜጋ ሁሉ የኑሮ ሁኔታ አስመርሮታል። በሀገሪቷ ተንደላቀው የሚኖሩት የወያኔ መሪዎችና ጭፍሮቻቸው ብቻ ናቸው። የፖለቲካና የኀሊና እስረኞችን የወኅኒ ቤት ስቃይና መከራስ ማን ሊያውቀው ይችላል?

- ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ከማንኛው ዘመን ታሪኩ በበለጠ የተጠቃ፥ የተናቀ፥ የተዋረደና የተጨቆነ ነው። ሀገሩም የተዋረደች ሆናለች።

- በሌላ በኩል ግን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት ሳይከፋፈል፥ አልገዛም ባይነቱን በጋራ እየገለፀ በየአቅጣጫው እየተዋደቀ ይገኛል። በሚሊዮን የሚቆጠረውና በመላው ዓለም የሚኖረውም ኢትዮጵያዊ በበኩሉ፥ የዲፕሎማሲ ትግሉን በኅብረት ከማካሄደ አልተቆጠበም። ለሀገር ቤቱ ትግልም፥ የገንዘብ ፥ የቁሳቁስና ሌሎቹንም ዕርዳታዎች ያደርጋል። ከሁሉም በላይ የሚያስደስተውና ለትግሉም ከፍተኛ አስተዋፅዖና ዕመርታ ሊሰጥ የሚችለው ደግሞ፥ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም እንደ ጥንቱ፥ በዘር፥ በቋንቋና በሃይማኖት ሳይከፋፈልና በነመለስ ዜናዊ ከፋፋይ ወጥመድ ሳይገባ፥ ተባብሮ በአንድ ላይ ሀገሩን ለማዳን መነሳሳቱ ነው። ይህን የተባባረ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል የሚበገረው እንደማይኖር ጠላቱም ሆነ ወዳጁ ሊጠራጠር አይችልም።

- ይንንን ሀቅ ተገንዝበው፥ መለስ ዜናዊን የሚደግፉ መንግሥታት ፖሊሲያቸውን እንዲያስተካክሉ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አጥብቆ ይጠይቃል። ለእነርሱም ቢሆን፥ ከወደፊቱ የረዥም ጊዜ ጥቅም አኳያ ሲታሰብ፥ ዕፍኝ ከማይሞሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ይልቅ፥ ወደ ሰማኒያ ሚሊዮን የሚጠጋውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘላቂ ወዳጅነት ማትረፍ፥ የአስተዋይ ዲፕሎማሲ ውጤት ይሆናል። ይህ ግን ባመረቃ ትግል የሚተላላፈላቸው መልዕክት መሆን አለበት። የሀገራችን ሕዝብ

ደግሞ በችግሩ ጊዜ ለቆመለት ሁሉ ባለውለታ እንደሆነ ያለፈ ታሪኩ ይመሰክርለታል። ኢትዮጵያ ሀገራችን በኢጣሊያ ፋሽስት ጦር ስትወረር፥ ወረራውን በመቃወም፥ ድምፃቸውን ያሰሙትን፥ የሩሲያን፥ የሜክሲኮን ፥ የዩናይትድ ስቴትንና አየርላንድን ወለታ ማን ይረሳል?

- የሰላማዊው ትግል ሂደት በሩ ከተዘጋ ዓመታት አልፎ፥ የህጋዊው ተቃውሞና እንቅስቃሴ ታፍኖ መገኘቱን ሁሉም ዜጋ ተረድቶታል። ስለሆነም፥ የትግሉ ሁለንተናዊ ገፅታና ዓይነት፥ ይዘትና አድማስ፥ ባኅርይና አቅጣጫ እየተለወጠ መምጣቱንና የኢትዮጵያ ሕዝብም ትኩረት ወደዚሁ የትግል ምዕራፍ እያነጣጠረ መሄዱንም ሁሉም የፖሊቲካ ጠበብቶች ይስማሙበታል። " ህግ የማይዳኘውን፥ ኃይል ይገዘዋል" የሚባለው ይትበኃል እንዲያው በከንቱ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ ሀገሩን ከዘረኞች ጥፋት ለማዳን በሚያደረገው ተጋድሎ፥ አሰፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንበትን የትግል ስልት የመጠቀም መብቱን ማንም ሊነፍገው አይችልም። በመሆኑም፥ የሀገሪቱም ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆናቸውን ሁሉም የፖለቲካ ተንታኞች ይስማሙበታል። ኢትዮጵያውያን ዛሬም እንደጥንቱ፥ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸውን ከማንም አይጠይቁም፥ አይለምኑም፥ አይጠብቁም። ያስራ ሰባት ዓመታት የጥቃትና የሰቀቃ እሮሯቸውን ከእነርሱ በስተቀር የማንም ደንታ አልሆነም። በአንድ በኩል፥ የእነርሱን ጩኸትና ሰቀቃ ሰማም አልሰማ ባዕዱ ዓለም፥ ምንም ለውጥ እንደማያስገኝላቸው ቢገነዘቡትም፥ በሌላ በኩል ግን እስካሁን ድረስ፥ በአንድ ልብ መገናኘት፥ በአንድ ቃልና ልሳን መናገር፥ አልተቻለም። ይህ ሁኔታ በአስቸኳይ መለወጥ አለበት። የኢትዮጵያን ጊዚያዊ ሁኔታ በመሠረታዊ መልኩ ለመለወጥና ብሎም ሀገሪቱን ከወያኔ የጎሳ አምባገነን አገዛዝ ለማዳን ከልብ ከታመነበት፥ የሚከተሉት ርምጃዎች በአፋጣኝ መከናወን ይኖርባቸዋል።

ሀ) ሁሉም ሚዛንና ክብደት ያላቸው ተቃዋሚ ድርጅቶች በጋራ ጉባዔ በመቀመጥ፥ ያለባቸውን ችግር አስወግደው፥ ጥርስ ያለው አዲስ ኅብረት በመፍጠር፥ የጋራ ሀገራቸውን ለማዳን አዲስ የትግል ስልትና ዕቅድ አውጥተው በጋራ መታገል አለባቸው። ያለፈውን ድክመትና ስህተት ፤ፀገምና ዕፀፅ እያነሱና እየጣሉ፥ እርስ በእርስም ጣት እየተጠቋቆሙ ጊዜን ማጥፋት፥ ወያኔን እንጅ ሌላ ማንንም አይጠቅምም።ትግሉ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሽጋገር ያለበት መሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወቅታዊ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን፥የሀገሪቱም ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚያስገድዱት እውነታ ነው።

ለ) ሌሎች የኅብረትሰብ ክፍሎችና የብዙኃን ድርጅቶች፥ የሲቪክ ማኅበራት፥ ደራስያን፥ ጋዜጠኞች፥ ምሁራንና፥ የሃይማኖት ተቋማት ወዘተ..... ሀገር በማዳኑ ሂደት ወስጥ የሚሳተፉበት ተገቢ መድረክ ሊመቻችላቸው ያስፈልጋል። ሁሉን ያላካተተ ሀገራዊ ትግል ግቡን

ባፋጣኝ ሊመታ አይችልምና!

ሐ) መለስ ዜናዊ “የሀገር ቤቱን ሁኔታ በሙሉ ተቆጣጥሪዋለሁ፥ አሁን ያስቸገረኝ ዲያስፖራው ብቻ ነው” ብሎ እየለፈፈ በመሆኑ፥ አሁን በውጭ ያለውን ተቃዋሚ ለማዳከም ለመከፋፈልና ከተቻለም ለማጥፋት፥ ከባዕዳን አለቆቹ ጋር በመመሳጠር ላይ ይገኛል። ይህንን ተገንዝቦ ወያኔን ተፃርሮ የቆመው ኃይል ሁሉ ተባብሮ፥ ክተት-መክት ብሎ መቆም አለበት።

ኢትዮጵያን አሁን ከገባችበት አዝቀት ለማውጣት በአንድ የጋራ ዓላማ ስር ተሰባስቦ በጋራ ድምፅና ልሳን መናገር አማራጭ የለውም። ወጣም ወረደም ግን በተጨባጭ ፀረ ወያኔው ትግል መፋፋም አለበት እንላለን።